ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ ጁማዳ አልአኺራ 25/1443 ሂ.
የአውቃፍ ሚኒስቴር ጃንዋሪ 28/2022 ግ.

# የሀገር ሙብትና ስለሱ መስዋእትነት መከፈል

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{وَاعْتَصِمُوا بِحَبْلِ اللَّهِ جَمِيعًا وَلَا تَفَرَّقُوا}

(የአላህንም (የማመን) ገመድ ሁላችሁም ያዙ፡፡ አትለያዩም፡፡)

አጋር የሌለው ብቸኛ አላህ እንጅ የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመስክራለሁ፡፡ ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡

ከዚህም በመቀጠል

ሀገር ሲባል ከነዋሪዎቹ ልብ ዘንድ ከፍተኛ ቦታ ያለው መሆኑይታወቃል፡፡ ሀገር ወዳድነት ቅን የሆነ የሰው ልጅ መንፈስ የተመሰረተበት የሰው ልጅ ተፈጥሮ ነው፡፡ አስመዒይ የተባሉት ሊቅ እንድህ ይላሉ፡ «የአንድን ሰው ቃል አክባሪና ቀል ኪዳን ጠባቂነቱን ለማወቅ ከፈለግህ ለሀገሩ ያለው ትውስታ፣ ለወንድሞቹ ያለውን ናፍቆትና ስለአለፈው ዘመኑ የሚያሰማውን ሮሮ ተከታተል»፡፡

የሀገር ፍቅርና ሀገራዊነት ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው፡፡ በመሆኑም ሀገር ውዳድነትን ማጠናከር ሀገርን ለማሳደግና ለማሻሻል መስራት የሚሉት ደንቦች በእስልምና አምነት ህግጋቶች በተደጋጋሚ ተጠቅሰዋል፡፡ እነሆ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ወደመዲና አልሙነወራ የስደት ጉዞ በጀመሩበት ሳዓት ወደሀገራቸው መካ ዞር አሉና እንድህ በማለት ተሰናበቷት፡ (አጅግ ደግ ሀገር ነሽ! እኔም በጣም እወድሻለሁ! ህዝቦችሽ ካንቺ ባያስወጡኝ ኖሮ ካንች ባልወጣሁ ነበር)፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) መዲና ገብተው በሷ መኖር ከጀመሩ በኋላ ደግሞ ይህችን ሀገር በልባቸው የተወደደች እንዲያደርግላቸው አላህ (ዐ.ወ.)ን እንድህ በማለት ለምነዋል፡ (ጌታችን ሆይ! መከን እንደምነወዳት ሁሉ ወይም ከዚያ በላይ መዲናን እንዲነወዳት አድርገን)፡፡

ይሁንና የሀገር ፍቅር ማለት በልሳናችን የምንሰነዝረው ቃል ወይም የምናነግበው መፍክር ብቻ አይደለም፡፡ ነገር ግን የሀገር ፍቅር ማለት ሥነ ምግባርና የምንወደውንና የምናደንቀውን ነገር መስዋእት የምንከፍልለት ክቡር ሀብት ነው፡፡ እውነተኛ ሀገራዊነት ማለት የእሱን ሉኣላዊነት በሚገባ ማክበርና እሱን ከልብ መውደድ፣ ለደህንነቱ፣ ለመረጋጋቱ፣ ለእድገቱና ለብልጽግናው ከፍተኛ ትኩረት መስጠትን እንድሁም መብትና ግዴታን ሙሉ በሙሉ ማክበርን ያካትታል፡፡ እውነተኛ ሀገራዊነት መስዋእትና ክብር ነው፡፡ ምክንያቱም ሀገራችን ለክብሩ፣ ለእድገቱና ለደህንነቱ መስዋእት እንድንከፍል ግድ ይለናልና፡፡

ከነዋሪዎቹ ለሀገር ካሉት መብቶች ተቀዳሚው ለሱ መስዋእት መከፈል የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ከሚከፈሉ መስእቶች ታላቅ ደረጃ ያለው ደግሞ ሕይወትን መስዋእት ማድረግ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{مِنَ الْمُؤْمِنِينَ رِجَالٌ صَدَقُوا مَا عَاهَدُوااللَّهَ عَلَيْهِ فَمِنْهُم مَّن قَضَى نَحْبَهُ وَمِنْهُم مَّن يَنتَظِرُ وَمَابَدَّلُوا تَبْدِيلًا}

(ከአማኞቹ በእርሱ ላይ ለአላህ ቃል ኪዳን የገቡበትን በእውነት የፈጸሙ ወንዶች አልሉ፡፡ ከነርሱም ስለቱን የፈጸመ (ለሃይማኖቱ የተገደለ) አልለ፤ ከነርሱም ገና የሚጠባበቅ አልለ፡፡ (የገቡበትን ቃል) መለወጥንም አልለወጡም፡፡)

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ለሀገር ዘብ የቆሙና ሀገርን የሚጠብቁ እነዚያም ሀገርን ለመከላከል ሕይወታቸውን አሳልፈው የሚሰጡ ሰዎች ከገሀነም እንደሚድኑ እንድህ በማለት አብስረዋል፡ (ሁለት ዓይኖች እሳት ከቶ አትነካቸውም፡፡ አላህን በመፍራት ያለቀስ አይንና በአላህ መንገድ ዘብ ቆሞ ያደረ ዓይን)፡፡ በመሆኑም መስዋእትነት የከፈሉ ሰዎች አላህ ከመረጣቸው ከምእምናን ወገን እንድሁም ከነብያት፣ ከፃድቃንና ከደጋጎቹ ጋር የመቀላቀል እድል አግኝተዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَلِيَعْلَمَ اللَّهُ الَّذِينَ آمَنُوا وَيَتَّخِذَ مِنكُمْ شُهَدَاءَ}

(አላህም እነዚያን ያመኑትን እንዲያውቅ (እንዲለይ) ከእናንተም ሰማዕታትን እንዲይዝ ነው፡፡) እንድሁም እንድህ ይላል፡

{وَمَن يُطِعِ اللَّهَ وَالرَّسُولَ فَأُولَٰئِكَ مَعَ الَّذِينَ أَنْعَمَ اللَّهُ عَلَيْهِم مِّنَ النَّبِيِّينَ وَالصِّدِّيقِينَ وَالشُّهَدَاءِ وَالصَّالِحِينَ وَحَسُنَ أُولَٰئِكَ رَفِيقًا

(አላህንና መልክተኛውንም የሚታዘዝ ሰው እነዚያ ከእነዚያ አላህ በእነርሱ ላይ ከለገሳቸው ከነቢያት፣ ከጻድቃንም፣ ከሰማዕታትም፣ ከመልካሞቹ ጋር ይኾናሉ፡፡ የእነዚያም ጓደኝነት አማረ፡፡)

****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትና ሰላም የነብያትና የመልክተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

በነዋሪዎቹ ላይ ለሀገር ከአሉ ግዴታዎች ሌላው ደግሞ ጥቅሙን ለማስከበር በተፈለጉ ጊዜ እነሱ ብርቱዎችም ደካሞችም ቢሆኑ ለመዝመት ዝግጁ መሆናቸው ነው፡፡ ነዋሪዎች በተፈለገው መልኩ ሀገርን ለመታደግ ሕይዎታቸውን የመሰዋትና

ደማቸውን የማፍሰስ ግዴታ አለባቸው ካልን የሀገርን ጥቅም ለማስከበር በሚያስፈልግበት ወቅት አዎንታዊ ተሳትፎ ማድረጋቸው ለሀገር ክብር፣ ለሀገር ፍቅርና ለገር ታማኝነት የሚደረግ ቀላሉ ትልእኳቸው ሊሆን ይገባል፡፡

ለሀገር ድህንነት የሚከፈል ግብር አንድ ትውልድ ብቻ ወይም ከፊሉ ነፃ ሆኑ ከፊሉ ነዋሪ የሚከፍለው ግብር አይደለም፡፡ ይልቅኑም ተከታታይ ትውልደና ሁሉም ወገን የሚሳተፍበት የጋራ ግብር የሚከፈልበት ተግባር ነው፡፡

ሌላው የሀገር ግዴታም ታታሪነት፣ ሥራና ጥራት የሚሉትን ጉዳዮች ያካትታል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አላህ አንዳችሁ ሥራን በሚያከናውንበት ወቅት በጥራት መስራቱን ይወዳል፡፡)

በተሰጠው ሃላፊነት ግዴታን መወጣት ሌላው የሀገር ግዴታ ነው፡፡ የምንግስት ሥራ አደራና በአንድ ሰው ትከሻ የተጣለ ሃለፊነት በመሆኑ ሥራውን በሚገባ ማከናወኑ ሃይማኖታዊና ብሄራዊ ግዴታ ሲሆን ይህን ግዴታ ከመወጣት መቦዘንና ቸል ማለት አደገኛ ከሚባሉት ብልሹነቶች አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው ምንጊዜም ልቡ ሕያውና አይምሮው ንቁ ሆኖ እንድህ የሚለውን የአላህን ቃል ዘወትር ማስታወስ ይኖርበታል፡

{وَهُوَ مَعَكُمْ أَيْنَ مَا كُنتُمْ وَاللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ. }

(እርሱም የትም ብትኾኑ ከእናንተ ጋር ነው፡፡ አላህም የምትሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነው፡፡)

የአንድን አገር ሰንድቅ ዓላማ፣ ብሄራዊ መዝሙር፣ አርማዎችና መፍከሮቹን ማክበር የነዋሪዎቹ ግዴታ ነው፡፡ ሰንድ ዓላማ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭም ያሉ ዜጎቹ የሚተሳሰሩበት የአንድ ሀገር አርማና መለያ ገጽታው ነው፡፡ በዚህ ሰንድቅ አላማ ስርም ውጤታማነትና ስኬታማነታቸውን ያረጋግጣሉ፡፡ ሀገረን ማክበር ከሀገር ግንባታ ቋሚና ተቀዳሚ አምዶች አንዱ ነው፡፡

ሌላው የሀገር ግዴታ ደግሞ በሀር ውስጥ፣ ከሀገር ውጭም እንድሁም በመላው ብሄራዊና ዓለም አቀፍ መድረኮች በተምሳሌነት አገርን መወከል እንድሁም ሰንደቅ

አላማው በየትኛውም ሀገር ከፍ ብሎ እንዲውለበለብና ሁሉም ግልሰብ ለሀገሩ ድንቅ አምባሳደር ለመሆን ከፍተኛ ጥረት ማድረግ የሚሉት ጉዳዮች ነው፡፡

ሁሉም ወገን የሀገሩ ምድር እንዲደፈር፣ እምቅ ሀብቱ እንዲነካና በቃለም ሆነ በተግባር እንዲደፈር ፈጽሞ አለመፍቀዱና በተፈለገው ሁኔታ ሀገርን በቃል መከላከል እንድሁም ጠላትን ለመመከት ሕይወትንና ሁሉንም ንብረት መስዋእት በማድረግ መጋፈጡ ሌላው የሀገር ግዴታ ነው፡፡

ጌታችን ሆይ! ሀገራችን ግብጽን እንድሁም መላ የዓለም ሀገራትን ከመጥፎ ነገር ሁሉ ጠብቅልን፡፡ አሚን፡፡